# ማውጫ

ገጽ


1. ማውጫ ……………………………………………………………………… 0
2. የተቋሙ መዋቅር……………………………………………………………… 1
3. መግቢያ……………………………………………………………………… 2
4. የ 2001 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ………………………..... 3-4
5. ራዕይ፣ተልዕኮ፣እሴቶችና፣ዓላማ…………………………………………… 5
6. ግቦች፤ቁልፍና፣ዓበይት የትኩረት መስክ ……………………………………… 6
7. የጽ/ቤቱ ግቦችና ውጤቶች…………………………………………………. 7
8. ቁልፍ ውጤቶች ………………………………………………………... 7-10
9. ዓበይት ውጤቶች…………………………………………………………. 11-12
10. ዓመታዊ ግቦች፣ ውጤቶች ፣ ስኬቶችና ፋይዳ አመልካቾች……………… 13-17
11.ዓወንታዊና አሉታዊ ታሳቢዎች…………………………………………… 18
12.የክትትል፣ሪፖርትና ግምገማ ሥርዓት…………………………………….. 18-19
13.የአቅ/ግ/ጽ/ቤት የ2002 መርሀ-ግብር ……………………………………… 20-28
14.የሰው ሀይልና የበጀት ዕቅድ…………………………………………….... 29
15.ዕቅዱን ያዘጋጀውና ያፀደቀው አካል ……………………………………… 30

1. <u>***መግቢያ፡-***</u>ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣትና ከልማቱም ህዝብ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሥርዓት ለመዘርጋትና መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ዲሞክራሳዊ ሥርዓት ለመገንባት የማስፈፀም አቅም ግንባታ ሥራዎች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ ፡፡

በመሆኑም የወረዳችን ህዝብ ከሚገኝበት ኂላ ቀርነትና ድህነት እንዲላቀቅ ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ያስመዘገብናቸው የልማት ውጤቶች ዘላቂ እንዲሆኑ ቀጣይነት እንዲኖራቸው በወረዳ የሚታዩ የማስፈፀም አቅም ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል የትኩረት መስክ ለይቶ በማስቀመጥ የአምስት ዓመት የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራተጂ የተዘጋጀ ሲሆን ይህንኑ ተከትሎ የ2002 ዓ/ም. በጀት ዓመት የዲራሼ ልዩ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ዕቅድ ተዘጋጅቷል ፡፡

በዚሁ መሠረት የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ባለፉት ዓመታት የተከናወኑ ተግባራትንና ያጋጠሙን ችግሮች በመገምገም የተገኙ ሀሳቦች ፣ አገራዊ የትኩረት አቅጣጫዎችን የሴክ ተሩ ስትራቴጂያዊ ግቦች በዋና ግብዓትነት ውለዋል ፡፡ በዚህ መሠረት በየደረጃው የሚታዩትን የማስፈፀም አቅም ችግሮች ደረጃ በደረጃ በመፍታት ያልተማከለ አስተዳደርን ማጠናከር ፣ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ለመፍታት የተጠቀሰው ስልት ተፈጥሮ በተግባር ላይ እንዲውል ማድረግና አጠላይ የሪፎርም ሥራዎችን በተጠናከረ መልኩ በማስተግበር በቅድሚ የመሠታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ወደ ትግበራ በማስገባትና በማድረግ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት ቁልፍ ሥራ ይሆናል ፡፡

በአጠቃላይ ሲታዩ የ2002 ዓ/ም. የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ዕቅድ ስትራቴጂያዊ ግቦችን መሠረት ያደገና የህዝባችን የሕብረተሰብ ክፍል ዲሞክራሲንና መልካም አስተዳደርደን ማስፈን ፐብሊክ ሴክተር አቅም ግንባታ ኘሮግራምችን በተቀናጀ ሁኔታ ማስፈፀምንና በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ተቋማት ሁለንተናዊ ለውጥ በማምጣት ቀልጣፋና ውጤታማ አሠራር መዘርጋትን የቅድሚያ ትኩረቱ አድርጓል ፡፡

ዕቅዱ ባለፉት ዓመታት በተፈፀመው መልኩ በወረዳ ደረጃ የሚገኙ አቅም ግንባታ ሴክተር መ/ቤቶች በየደረጃው እንዲካሄድ በማድረግ የሚተገበር ይሆናል ፡፡

## 2 የ 2001 ዓ.ም የሴክተሩ ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ

የወረዳው አቅም ግንባታ ሴክተር የ2001 ዓ.ም በጀት ዕቅድ ሲዘጋጅ ስትራቴጂክ ዕቅድ መነሻ ማድረግና ባለፉት ዓመታት የተከናወኑ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች አፈፃፀም ያጋጠሙትን ችግሮች በመገምገም በዓመቱ የሚተገበሩ ግቦችን ለይቶ በማስቀመጥ የታቀደ ሲሆን ያልተማከለ አስተዳደር ማጠናከር በየደረጃው የማስፈፀም አቅም ግንባታ በክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት ፤ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች የሚፈቱበትን ስልት መቀየስና አጠቃላይ ፐብሊክ ሴክተር የሪፎርም ፕሮግራም ሥራዎችን በተጠናከረ መልኩ ለመተግበር መንግሥታዊ መ/ቤቶች በራሳቸው ላይ ለውጥ በማምጣት የማስፈፀም አቅማቸውን መገንባት ቁልፍ ሥራ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ለዚሁም የሴክተሩ ዋናዋና ችግሮች በመፍታት በራሱ ላይ ለውጥ በማምጣት የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ቀጣይነት ባለው መልኩ በወረዳ እንዲተገበሩ ማድረግ በዕቅዱ ውስጥ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ከተቀመጡ ግቦች የተከናወኑት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ✓ በሪፎርሙ ሥራ ላይ እምነት ፈጥረው የሚንቀሳቀሱ 30 ከፍተኛ አመራት/የጽ/ቤት ኃላፊዎች/ ቢሆኑም አብዛኛዎቹ ወደ ሪፎርሙ ሥራ ፈጥኖ ለመግባት አልቻሉም፡፡
- ✓ የሪፎርሙን ሥራ ውጤታማ ማድረግ የቻሉ ከ 50 መካከለኛ አመራች እና 200 ሠራኞች ግማሾቹ ወደ ሪፎርሙ ፕሮግራም ፈጥነው የገቡ ሲሆን ግማሹ ገና ሊሠሩባቸው የሚሆን ጉዳይ ይሆናል
- ✓ በየሩብ ዓመቱ አንድ ጊዜ የተደረገ የሪፎርም ሥራ ግምገማ ውጤት፡፡
- ✓ በመልካም አስተዳደር ረገድ አጋዥ የሆነ የሪፖርት የቅሬታ ማቅረቢያ የቅሬታ መልስ መስጫና ሌሎችም ቅፃቅፆች ለ 28ቱ ቀበሌያትና ለ20ዎቹ ጽ/ቤቶች የተላ ቢሆኑም እየተጠቀሙ ስላልሆነ ወደ ትግበራ እንዲሸጋገሩ ያላሰለሰ ጥረት ይጠይቃሳ፡፡
- ✓ በ20 ጽ/ቤቶች የተደረገ የመልካም አስተዳደር የሪፎርም ሥራ መጠነኛ ክትትል
- ✓ በ15 ቀበሌያ የተዘረጋ የህ/ሰብ ተሳትፎ/ስልክ/ ልውውጥአገልግሎት
- ✓ የፀረ ኤች አይ ቪ ኤድስን እንቅስቃሴ በማጠናከር የቫይረሱን ሥርጭት ለመግታት የተደረገጥናት እና ሴክተሮች መዋጮ የሚያደርገው ድጋፍም ተጠናክሮ እየሄደ ይገኛል፡፡

2. <u>*ያጋጠሙ ችግሮች*</u>

በአጠቃላይ ሴክተሩ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት በሚደረገው ጥረት በርካታ ችግሮች ያሉበት ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ ቀጥለው የተቀመጡ ናቸው፡፡

1. በአቅም ግንባ ስትራቴጂ ፕሮግራሞችና በማስፈፀም ስልት ላይ ባለሙያ ሙሉ በሙሉ አለመኖር
2. ከአስቀጣይ ሴክተር መ/ቤቶች ጋር የግንኙነትና የቅንጅት ችግር መኖር
3. ለዕቅዱ ማስፈፀሚያ የሚሆን በቂ በጀት አለመመደብ እና የበጀት እጥረት ቀጣይ መሆን
4. የሴክተር መ/ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አለመሆን
5. የተጠናከረና የተቀናጀ የዕቅድ አፈፃፀም ሥርዓት አለመኖርና በፀደቀ ዕቅድ አለመመራት
6. በወረዳው በቆላ ቀበሌያት በተከሰቱት ግጭቶችና አለመግባባት የተቻለውን ያህል እንዳይሰሩ ማድረጉ
7. ለጽ/ቤቱ ምንም ተሽከርካሪ ያለመኖር የቢሮ ቁሳቁስ የሰው ኃይልና የሥራ ቦታ አለመሟላት
8. በሴክተሩ የተጠናከረ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ እንዲሁም የተገኙ ውጤቶችን ለኅብረተሰቡ የማሳወቅ ሥርዓት አለመኖር
9. የከፍተኛ መካከለኛ አመራሮች ተነሳሽነት ማጣት
10. የኢንተርኔትና የኢ-መይል አገልግሎት ዕቃዎች መበላሸትና ከተጠገነም በኃላ አገልግት ያለመኖር

- በአጠቃላይ የ2002 በጀት ዓመት ዕቅድ ከላይ በዝርዝር የቀረቡ የጽ/ቤትና የተቋማት ችግሮችን ደረጃ በደረጃ ለመፍታትና አጠቃላይ የጽ/በቱን ዓላማ ግቦች ለማሳካት ቁልፍና ዓበይት የትኩረት መስኮች ተለይተዋል ዝርዝር ግቦች በማስቀመጥ ለእያንዳንዱ ግብ ዝርዝር ውጤት ተነድፋል፡፡ ስኬትና ፋይዳ አመልካቾች ለግምገማ አመቺነት ቅድመ ትንቢያ ነጥቦች ተለይተው የአፈፃፀም መርሃ ግብር ተዘጋጅቷል ለግቦች ማስፈፀሚያ በጀትና የሰው ኃይል ዕቅድ እንዲካተት ተደርጓል የክትትል ግምገማ ስልት ተቀይሷል አዎንታዊና አሉታዊ ታሳቢዎች ግምት ውስጥ እንዲገባ ተደርጎ ዕቅዱን ለሁሉም ጽ/ቤቶች የተቀናጀ በማድረግ ለግብ ስምምነት መፈራረም በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡

## የጽ/ቤቱ ራዕይ /Vision/

ልዩ ወረዳችን በሚቀጥሉት አምስት ዓመትት በ2007 የተቀናጀ ተቋማዊ አቅም በመገንባት ድህነትን በመቀነስና ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ በሁለንተናዊ መልኩ ያደገና በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች ሞዴል ሆና ማየት፡፡

## የጽ/ቤቱ ተልዕኮ/Mission/

የአገራችንን የማስፈፀም አቅም ግንባታ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን መሠረት በማድረግ የወረዳውን የተቋማዊ የሰው ኃይል አሠራርና አደረጃጀት በማሻሻልና የህ/ሰቡን የተገልጋይነት መንፈስ በማጎልበት ቀጣይነት ባለው ፈጣን የኢኮኖሚ ልማትና የድህነት ቅነሳ ግብ መሳካት ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መልካም አስተዳደር መስፈን ተግባራዊ የሚያደርግና ለለውጥ የተዘጋጀ ተቋም አመራርና ሲቪል ሰርቫንት መፍጠር

## የጽ/ቤቱ እሴቶች/Core Values/

1. ቀልጣፋ ውጤታማ ጥራት ያለውና ወጪ ቆጣቢ አገልግሎትእንሰጣለን
2. ለጋራ ራዕይና ተልዕኮ መሥራት
3. ለመልካም አስተዳደር መስፈን የፀና እምነት
4. ለውጤት መሥራት
5. ግልፅነትና ተጠያቂነት ማስፈን
6. የህዝብ አገልጋይነትን ማጎልበት
7. የአቅም ውስንነትን ማስወገድ
8. ያለመረጃ ማቀድ ማስቀረት
9. ለውጥ መቀበልና መስጠት
10. የተገልጋዬቻችን ችግር ፈቺዎች ነን
11. ከተገልጋዬቻችን ጋር በጋራ አቅደን በጋራ እንፈጽማለን
12. ውጤታችንም ውድቀታችንም የጋራ ነው
13. ሥራችንን በታማኝነት መፈፀም
14. የምንለካው ውጤት ነው በውጤታችን እንመዘናለን

## የጽ/ቤቱ ዓላማ/Objectives/

የመንግስት ተቋማትን የማስፈፀም አቅም በመገንባት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት በማረጋጥ በመልካ አስተዳደር እመርታ ማምጣት

## የጽ/ቤቱ ግቦች /GoALS/

**ቁልፍ**

1 የ/BPR/ አፈፃፀም የተሟላ የሆነበት አሠራር ተፈጥሮአል

2 በሁሉም ሴክተሮች /ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ ሚዛናዊ ውጤት ተኮር ዕቅድ// አሠራር ተዘርግቷል

3 በሁሉም ሴክተሮች /ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የቅሬታ መስተናገጂያ ሥርዓት

4 ከወረዳችን እስከ ቀበሌ ድረስ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ ተዘርግቶ ሥራ ላይ የዋለ የኢንስፔክሽን ሥራ

5 በ28ቱም ቀበሌያመዋቅሮች አሳምኖ ማሰራት መርህ መደገፍና ለማብቃት የተሠራ ሥራ

6 በፍትህ ሴክተሩ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራሙ አተገባበር በተገቢው እንዲፈፀም የተደረገ ድጋፍና ክትትል

7 በመልካም አስተዳደርና በሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራሞች አተገባበር ላይ ስኬቶችንና ውድቀቶችን የመለየት አንድ ጥናት

8 በወረዳው የተዘረጋና የተስፋፋ የኢኮቴ መሠረተ ልማት ወረዳ ኔት ስኩል ኔት Wan:Lan ማህበረሰብ መረጃ ምዕከል

9 አስቀጣይ ተቋማትን የማስፈፀምን አቅም ለማሳደግ የተፈጠረ አቅም

10 100%በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የተደራጀ የመንግስት ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ

11 100% የተፈቱ አስተዳደራዊ የአፈፃፀም ችግሮች/ቅሬታ ወዘተ

12 በሥልጠና የጎለበተ የወረዳውና የቀበሌአት በቁጥር አመራሮችና ባለሙያዎች

13 የጽ/ቤቱን አሠራር ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የተገነባ የኢኮቴ ህንፃ

**ዐበይት**

1 በወረዳው የመንግስት ተቋማት የተዘጋጀ የተቀናጀ የልማት ዕቅድ እና በወቅታቸው የተሰራጩ ሪፖርቶች

2 በጽ/ቤቱ ተግባራዊ የሆነ የሥርዓተ ፆታና ኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥራ

3 በአቅ/ግ ፕሮግራሞች ላይ ለህ/ሰቡና ለሴክተሮች የተሰራጨ የጽ/ቤቱ ወቅታዊ መረጃዎች

4 ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም ክፍተቶች ለመሙላት የተደረገ አንድ ዳሰሳ ጥናት

## 3. የሴክተሩ/የጽ/ቤቱ ግቦችና ውጤቶች

➢ በቁልፍ የትኩረት መስክ

1. በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥና ሙሉ ትግበራ የተሟላ አሰራር ላይ መድረስ
   - ከ /BPR/ ጋር የተጣጣመ የሥራ ምዘናን ደረጃ አሰጣጥ ሥርዓት ተፈጥሮአል፡፡
   - በውጤት ተኮር ላይ የተመሠረተ የማትጊያ ክፍያ ሥርዓት ተፈጥሮአል፡፡
   - የማወዳደሪያ ዕውቅናና የማበረታቻ ሥርዓት ተፈጥሮአል፡፡
   - አስፈፃሚ አካላት መልሶ ለማደራጀት ከክልል የሚወርድ አዋጅና ደንብ ተተግብረዋል፡፡
   - ከኃላፊነት የሚነሱ ተሿሚዎች ጥቅማ ጥቅም የማስጠበቅ ሥርዓት /በክልልበሚወርድ አሠራር መሠራት
   - በ2ኛ ዙር /BPR/ የሚተገበሩ ተቋማት ሠራተኞች 100% ስልጠና አገኙ፡፡
   - በሁሉም ተቋማት የ/BPR/ ትግበራ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡
2. በሁሉም ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ ሚዛናዊ ውጤት ተኮር አሠራር ሥርዓት
   - በውጤት ተኮርአሠራሩን ከክልል በሚወርደው መሠረት ተግባራዊ ሆኗል /ሰነድ ሥልጠና...../
   - ስለውጤት ተኮር አፈፃፀም በሴክተሮች የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል
3. ከወረዳው እስከ ቀበሌ ድረስ በመልካም አስ/ር እምርታ ታይቷል፡፡

   3.1 በሁሉም ሴክተሮች የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት
   - የተጠናከረ በየቀበሌው ደረጃ የተዘረጋ የቅሬታ ማስተናገጃ የመረጃና የጉዳይ አቀባበል አሠራር ሥርዓት
   - የገጠር ልማት ተግባሮች በቀበሌ ደረጃ ተጣምረውና ተቀናጅተው ወደ ተግባር የሚወርዱበት የእቅድ አዘገጃጀትና ሪፖርትአቀራረብ አሠራር
   - በቀበሌያቱ አራት የልማት ኮሚቴዎች በተቀናጀ ሁኔታ የሚሰሩበትን አሠራር በተጠናከረ መንገድ የቀጠለ
   - በ 28ቱም ቀበሌያ የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ እንዲጠናከር የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ ድጋፋዊ ክትትል

3.2 ከወረዳው እስከ ቀበሌያት ድረስ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋ የኢኒስፔክሽን ሥርዓት

- ከክልል የተቀበልነው የኢኒስፔክሽንና የሱፐርቪዥን መመሪያ ሥራ ላይ ዋለ
- ከክልል የተቀበልነው የኢኒስፔክሽንና የሱፐርቪዥን የአሠራርና የሥልጠና ሰነዶች እና የተወሰደ ሥልጠና
- በ 28ቱም ቀበሌያ በፓኬጅ መሠረት የተቋቋመና ሥራ የጀመረ የኢኒስፔክሽን ቡድን

3.3 በ28ቱም ቀበሌያ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ አሳምኖ በማሰራት ተፈፀመ

- ሞዴል ግለሰቦች መንደሮችና ቀበሌያ እንዲመረጡ ቴክኒካዊ ድጋ ተደርጓል
- የቀበሌ ም/ቤት የብዙሀን ማህበራት እንዲሁም ባህላዊ ተቋማት ተሳትፎን ለማጎልበት አራት ጊዜ የተሰጠ ድጋፍ
- በወረዳ ደረጃ አንድ ጊዜ የተደረገ የምርጥ ተሞክሮ ሰነድ ተዘጋጅቷል

3.4 በፍትህ ሴክተሩ የፍ/ሥ/ማሻ/ፕሮግራም አተገባበር በተገቢው እንዲፈፀም የተደረገ ክትትልና ድጋፍ

- ከክልል ጋር በመሆን ለፍትህ ተቋማት አሰራራቸውን ለማሻሻል የተደረገ የመሣሪያ ድጋፍ
- የዕለት ፍርድ ሥርዓት እጅ ከፍንጅ በተያዙ ወነወጀለኞች ላይ እንዲፈፀም የተደረገ ሁለት ጊዜ ድጋፋዊ ክትትል

3.5 100% የተፈቱ አስተዳደራዊ የአፈፃፀም ክፍተቶች/ቅሬታ  አቤቱታ /

- ለቀረቡ ቅሬታዎች ተጣርተው የተሰጡ ውሳኔዎች
- ለቀረቡ ቅሬታ በሥፍራው በአካል ተገኝተው የተጣራና የተሰጠ ውሳኔ
- በአካ ተገኝቶ ማስረጃ ማጣራትና በተዘዋዋሪ ችሎት የተሰጠ የይግባኝ ውሳኔ

4. በመልካም አሰ/ር በሲ/ሰ/ሪ/ፕሮ አተገባበር ላይ ስኬቶችና ክፍተቶችን የመለየት አንድ ጥናት ተደርጓል

5. በወረዳው የተዘረጋና የተስፋፋ የኢኮቴ መሠተ ልማት /ወረዳኔት ስኩል ኔት የማህበረሰብ መረጃ ማዕከል WAN/
   - ከክልል የተገኙ ኮምፒውተሮችና ተጓዳኝ ዕቃዎች እና የተደረገ ጥናት በቁጥር 10 ኮምፒውተሮች…/
   - ከሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች የተውጣጡ በቁጥር 31 አመራሮች እና 49 ባለሙያዎች በመሠረታዊ የኮምፒውተር አጠቃቀም ሥልጠና የወሰዱ
   - ለሴክተሩ መ/ቤቶች አራት ጊዜ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል

6. የአስቀጣይ ተቋማት የማስፈፀም አቅም ለማሳደግየተፈጠረ አቅም
   - የለውጥ አመራር ሥልጠና ከክልል የተቀበሉ ሁለት ባለሙያዎችና ለወረዳው አመራች የተሰጠ ሥልጠና
   - የኢኮቴ ቁሳቁስ በሴክተሮች እንዲሟሉ የተደረገ ድጋፍ
   - ለሰው ሀብት ሥራ አመራር የሥራ ሂደት ፈፃሚዎች በ ስራው ዙሪያ የተሰጠ ሥልጠና
7. 100% በዘመናዊ መረጃ አያያዝ የተደራጀ የመንግስት ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ
   - ወቅቱን ጠብቀውና በአግባቡ ተደራጅተው የተቀመጡ የሰው ኃይል መረጃ
   - ለተገልጋዬች የተሰጡ አግባባዊ መረጃዎች
8. በሥልጠና የጎለበተ የወረዳውና የቀበሌያ አመራሮችና ባለሙያዎች በቁጥር-------
   - የለውጥ አመራር ሥልጠና ያገኙ የወረዳው በቁጥር 31 አመራሮች 100 ባለሙያዎች
   - በ BSC ከአመራርና ባለሙያዎች 40 ና 60 የተሰጠ ስልጠና
   - ምደባ ያላገኙና ተመልምለው ወደ ትምህርት ተቋማት የገቡ ሠራተኞች
   - በሰው ሀብት ልማት ስትራቴጂ መመሪያ ላይ ሥልጠና የወሰዱ በቁጥር 2 ባለሙያዎች
   - ለሰው ሀብት ልማት ለለውጥ ፕሮግራም አስተባባሪዎች በክልል ደረጃ የተሰጠ ሥልጠና

- የአገር ውስጥና ውጭ ዕድሎች ላይ ስልጣኞች ከክልል ጋር ሆኖ በማፈላለግ ሥራ ላይ ውሏል
- ለ 26 የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች በመንግስት ፖሊሲዎች ፕሮግራሞች ….. ላይ የተሰጠ አንድ ሥልጠና
- ለ 200 የመንግስት ሠራኞች በመንግሥት ፖሊሲዎች ፕሮግራሞችና …. በ/BPR/ ላይ የተሰጠ አንድ ስልጠና
- ለ 20ዎቹ ሴክተሮች ተቋማትና ለ 28ቱ ቀበሌያ በክልል ደረጃ ተዘጋጅተው የሚመጡ መመሪያዎችና መስፈርቶች ተዋውቀው ተሠራጩ

9. የጽ/ቤቱን አሠራር ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የተገነባ የኢኮቴ ህንፃ
10. በምኅንድስና የአቅ/ግ/ፐሮ የመንግስትና የግሉን ሴክተር ለማጠናከር የተሠራ ሥራ
    - ተቋማት በቅንጅት የእሴት ሰንሰለት እንደሚመጡና እንዲተገበሩ ሁለት ጊዜ የተደረገ ድጋፍ
11. ግብርናና ገጠር ልማትን ማዘጋጃ ቤት ሥራ አመርታዊ ለውጥ እንዲያመጡ ከማድረግ አኳያ የተደረገ የአቅ/ግ/ ድጋፍ
    - በጥቃ/አነ/ተቋም ለተደራጁና በሥራ ላይ ላሉ ሰዎች የተሰጠ ድጋፍ
    - ተቋማት በቅንጅት የእሴት ሰንሰለት እንዲተገበሩየተደረገ ድጋፍ
    - በወረዳው የተዘረጋ የኔት ወርክ ዝርጋታ ማዘጋጃ ቤትንም በአገልግሎት አሰጣጥ እንዲረዳው የተደረገ ድጋፍ ይህም የሶፍት ዎርና የድረ ገጽ ሥራዎችን በመሥራት የመረጃ አያያዝና አሠራር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ ነው
    - የግብር አሰባሰብ ሥራ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲከናወን የተደረገ ድጋፍ
    - የተዘረጋ የአርሶ አደሩ የገበያ መረጃና የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሥርዓት
    - ከማህበረሰብ መረጃ ማዕከል የተጠቀሙ የገጠርና የከተማ ህ/ሰብ

➢ <u>በዐበይት የትኩረት መስኮች</u>

1. በወረዳው የመንግሥት ተቋማት የተዘጋጁ የተቀናጁ የልማት ዕቅድ ሪፖርቶች
   - የተዘጋጀ ስትራቴጂክ ዕቅድ እና የዓመት ዕቅድ/ በሁሉም ተቋም/
   - በሁሉም ተቋማት የተዘረጋ የአፈፃፀም ሪፖርት አቀራረብና የግንኙነት ሥርዓት
2. በጽ/ቤቱ ተግባራዊ የሆነ የሥርዓተ ፆታና ኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥራ
   - የጽ/ቤቱን ሠራተኞች በጉዳዩ በተከታታይነት ውይይት አድርገው የተገኘ ውጤት
   - ለጉዳዩ የተደረገ ተቋማዊ የበጀት ድጋፍ
3. በአቅ/ግ/ፕሮግራሞች ላይ ለህ/ሰቡና ለሴክተሮች የተሰራጩ የጽ/ቤቱ ወቅታዊ መረጃዎች
   - ተዘጋጅተው የበረሩ በራሪ ጽሁፎች በዓመት አንድ መጽሄት
   - በጉዳዩ ዙሪያ በመገናኛ ብዙሀን የተሰራጨ መረጃ በሥርዓተ ፆታም
4. ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም ክፍተቶችን ለመለየት የተደረገ አንድ ዳሰሳ ጥናት
   - የተካሄደ የሥልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት
   - የተለያዩ የሥልጠና ርዕሶች ላይ የተዘጋጁ ሰነዶች
   - ሌሎችም ከክልል ጋር ተገናኝተው የተሰሩ ሥራዎች

➢ <u>በንዑሳን የትኩረት መስኮች</u>

1. በቁጠባና በአግባቡ ሥራ ላይ የዋሉ ግብአት
   - የጊዜ አጠቃቀም ሥርዓት ተሸሽሎ ተገኘ
   - በግልይነትና በመረጃ የተደገፈ የዐላቂ ዕቃዎች አጠቃቀም በጀትን ጨምሮ
2. በአግባቡ ተግባራዊ የሆኑ የጽ/በቱ የተለያዩ የውይይት መድረኮች
   - የጽ/ቤቱ የማኔጅመንት የስታፍና ...........
3. ለተገልጋዩች የሚጠቅሙ መረጃዎች ታፔላ በተገቢው ቦታ ተለጥፈዋል
   - የግቢ ውስጥ የበር ላይና የቢሮ ውስጥ ታፔላዎች
   - ተገልጋይ ለማገልገል ማሟላት ያለበትን ቅድመ ሁኔታ
4. በተቻለ መጠን የተፈፀሙ ደራሽ ሥራዎች
   - በኮሚቴ አባልነት የተሠሩ ሥራዎች
   - ሳይታሰቡ በተደረጉ ጥሪዎች ላይ በመገኘት የተሰሩ ሥራዎች

5. ወደ ጽ/ቤቱ የመጡና ምላሽ ያገኙ የተለያዩ ትዕዛዞች ጥያቄዎችና .......... ምላሽ አግኝተዋል

- ከክልል ሴክተሮችን ለመጡት ተገቢውን ምላሽ ተሰጠ
- ከወረዳችን ከሌሎች ወረዳዎች ለመጡ ተገቢ ምላሽ ተሰጠ
- ከቀበሌያት
- ከግለሰቦች

6. ማስታወቂያ ቦርድ ማዘጋጀትና በምቹ ቦታ ተተክሎ አገልግሎት ሰጠ፡፡

__አዎንታዊና አሉታዊ ታሳቢወች__

__አዎንታዊ ታሳቢወች__

- የተሻለ የሰው ኃይል በመኖሩ ለተሻለ ውጤት ይመራናል
- የፀጥታ ችግር እየተቀረፈ ያለ መሆኑ
- ሁሉም ተቋማት በ BPR ወደ ሙሉ ትግበራ መግባታቸው
- ክልሉ ከዕቅድ ጀምሮ እስከ ክትትልና ድጋፍ አብሮን መሆኑ

__አሉታዊ ታሳቢዎች__

- ከ BPR ሥራ በአመራር ዘንድ የትኩረት ማነስ
- የመደበኛ በጀት ማነስ
- በሴክተሮች በቂ የሰው ኃይል አለመኖር
- የኢኮቴ / ICT / ዕቃዎች እጥረትና ለጊዜው የማሠልጠኛ ቦታ ማጣት
- በተለይ ለገጠር ላይ ሥራ ተሽከርካሪ ማጣት
- ከልማዳዊ አሠራር ቶሎ ያልተወበት መሆኑ
- የደጋ ቀበሌአት አከባቢ ዕቅዳችን ከመዋቅር አለመጠናከር ጋር ተያይዞ ለሥራ ሊከብደን ይችላል

__የክትትል ፣ ሪፖርትና ግምገማ ሥርዓት__

እንደ ሴክተር /ተቋም ዕቅዱ ተግባራዊ ሆኖ ፋይዳ ሊኖረው የክትትል ፣ ሪፖርትና ግምገማ ሥርዓት የግድ ይላል፡፡

በዚሁ መሠረት በሚከተለው መልኩ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

የክትትልና ሪፖርት ሥርዓት

ምን፣ መች፣ በምን ያህል ፣ በማን ፣ እንዴት---- ሥራዎች እየተተገበሩ እንዳሉ መከታተልና በመቀመር በተገቢው ግብአትነት ማዋል ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በመነሳት ለጠንካራ ጉኖች ማበረታቻ እና ድክመቶችን የመቅረፍ ሥራ ይሠራል፡፡

የክትትሉ ዋናው ነጥብ ሥራው በስታንዳርድ መሠረት መሠራት አለመሠራቱን ማጣራት ነው፡፡ ይህንንም ሥራ በአካል በመገኘትና በሚቀርቡ ሪፖርቶች አማካይነት የምንፈጽም ሲሆን በተለይ በ BPR ሥራ እስኪሰርጽ ድረስ በየ15 ቀን ሴክተራችን ሌሎችን ሴክተሮች በአካል ተገኝቶ ይከታተላል፡፡በየወሩ በጉዳዩ በጋራ በወረዳ ደረጃ መወያየትም ይጠበቅብናል፡፡ በየተቋማቱ ቢያንስ በሳምንት በአፈፃፀማቸዉ ዙሪያ ይወያያሉ፡፡

ከዚህ አኳያ ፡-

1. ወቅታዊ ሪፖርቶችንና መረጃዎችን ተጠቅመን ፣
2. በየትኩረት መስኮች በአካል ተገኝተን ቴክኒካዊ ድጋፍ በመስጠት
3. በየወሩ አንድ ጊዜ ወረዳዊ በሪፎርሙ ዙሪያ ውይይት ቢያንስ እስከ ጥር 2/2002 ይቀጥላል፡፡
4. በተቋማችን በየቀኑ ፣በየሳምንቱና በየወሩ እየተገናኘን መወያየት
5. በአጠቃላይ አስፈላጊ በሆነ ጊዜና በተቻለን መጠን ሁሉ ግንኙነት በመፍጠር ችግሮችን እየለዩ መፍትሔ ማምጣት ያስፈልጋል፡፡

<u>የግምገማ ሥርዓት</u>

ውጤትንና ስኬትን መለካት በሚያስችል የጊዜ ስፋት ውስጥ ሊከናወን ስለሚገባው በየሩብ ዓመቱ አንድ ጊዜ ይከናወናል፡፡ ይህም በክትትልና ሪፖርት ከሚገኙ መረጃዎች ተነስተን የምንፈጽመው ነው፡፡

በአጠቃላይ ለውጤታማ ሥራ ከሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመናበብና በዕውቀት ላይ ተመስርተን ልንፈጽመው ግድ ይለናል፡፡

ክትትሉም ሆነ ግምገማው ከውጤት ፣ ስኬትና ፋይዳ/ለውጥ አመልካቾች ተነስተን ነው መፈፀም የሚገባን